ጁን 8ቀን 2020ዓ.ም.

በዚህ የተለየ ጊዜ የተማሪዎችን ቀጣይነት ያለው ትምህርት ለመደገፍ FCPS የመማሪያ ጥቅሎች/እሽጎች በበጋ ወራት ለቅድመ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ጥቅም ላይ እንዲውል ያድላል። በጥቅሉ/እሽጉ ውስጥ ያሉት ተግባራት የተማሪዎችን ተሳትፎ ፣ ወሳኝ አስተሳሰብ እና የእንቅስቃሴ ፍላጎቶችን የሚደግፉ ሲሆኑ ለተማሪዎች እንዲለማመዱ እና ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ እድል ይሰጣቸዋል። የቀረቡት ተግባራት በቤትዎ እና በማህበረሰብዎ ውስጥ በቀላሉ እንዲተገበሩ የተቀየሱ ናቸው።

የ ESY መስፈርትን ያሟሉ ተማሪዎች በጥቅሉ/እሽጉ ላይ በመመርኮዝ ትምህርት እንዲያቀርብ አንድ መምህር ይመደባል። በ IEP ውስጥ በተዘረዘሩት መሰረት ወሳኝ የህይወት ችሎታዎች እንዲቀጥሉ ለማድረግ ተማሪዎች በተናጠል እንዲማሩ ይደረጋል።

ጥቅሉ/እሽጉ እንዲሁ በBlackboard 24-7 ላይ ይለጠፋል።

“ጨዋታ የልጆች ሥራ ነው።” - Irene Sege

የልጅዎን ትምህርት በተሻለ ለመደገፍ በየቀኑ ከልጅዎ ጋር ለመጫወት ጊዜ ይመድቡ። ከልጅዎ ጋር የሚያደርጓቸውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ማዳበሩ ወጥነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል እንዲሁም ትምህርታቸውን ይደግፋል።